ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ
የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 366(1)፣ 367(1)፣370፣393(1) እንዲሁም በተሻሻለው የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀፅ 16(1) መሠረት የግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 30ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤና 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ጎዳር 26 ቀን 2019 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ጀምሮ ቦሌ ሜጋ ወይም ሱር ኮንስትራክሽን ሕንፃዎች ጀርባ ዲቦራ ፋውንዴሽን ጎን በሚገኘው የኩባንያው አዲሱ ህንፃ ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤ ላይ በተባለው ቀን ሰዓትና ቦታ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል።

1. **የአክሲዮን ማህበሩ የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች**
   - 1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ስም ፡- ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር
   - 1.2 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ፣ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 01 ሱማሌ ተራ ግሎባል ሕንፃ ላይ ይገኛል።
   - 1.3 የማህበሩ ድህረ ገፅ WWW.globalinsurancesc.com
   - 1.4 የንግድ ምዝገባ ቁጥር አአ/ግማ/23372/39
   - 1.5 የመድን ሥራ ፈቃድ ቁጥር 008/97
   - 1.6 የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 368,676,000
   - 1.7 የማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 368,676,000
2. **የ30ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**
   - 2.1 እስከ ህዳር 25 ቀን 2019 ድረስ በነባር ባለአክስዮኖች የተገዙ አዳዲስ አክስዮኖች እና የአክስዮን ዝውውሮችን ማሳወቅ፤
   - 2.2 እ.ኤ.አ በ2025/26 በጀት ዓመት የዳሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፤
   - 2.3 እ.ኤ.አ የ2025/26 የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ፤ መወያየትና በቀረበው ሪፖርት ላይ ውሳኔ ማሳለፍ፤
   - 2.4 እ.ኤ.አ የ2025/26 የትርፍ ክፍፍል ላይ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ማፀደቅ፤
   - 2.5 እ.ኤ.አ የ2025/26 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ክፍያ መወሰን፤
   - 2.6 እ.ኤ.አ የ2026/27 የዳይሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል መወሰን፤
   - 2.7 እ.ኤ.አ ከ2026/27 የውጭ ኦዲተሮችን መሾምና ዓመታዊ ክፍያቸውን መወሰን፤
   - 2.8 የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ሪፖርት ማዳመጥ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ማካሄድ፤
3. **14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**
   - 3.1 እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30/2026 ድረስ የተፈረመው ክፍያ ያልተፈፀመባቸውን አክሲዮኖች መሰረዝ
   - 3.2 የማህበሩን መመስረቻ ጽሑፍ አንቀፅ 5፤አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 ካፒታልንና አክሲዮኖች በተመለከተ እንደዚሁም አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (1)፤ (2) እና (4) ማሻሻያ ማድረግ፤
   - 3.3 የጉርሻ አክሲዮን (Bonus Share) በተመለከተ ተወያይቶ መወሰን
4. **ማሳሰቢያ**

4.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸውን ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሠረት ጉባኤው ከማካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋናው መስሪያ ቤት 4ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ አላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካይም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችል መሆኑን እንገልፃለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው።

4.2 የአክሲዮን ማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ወይም ፋይዳ መታወቂያ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸው የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈ መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

የግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ
ዳይሬክተሮች ቦርድ